# <u>ቁራና ዕንቁራሪቶች</u>

"ዕልልታን ከሚያበዙ ዕንቁራሪቶችስ፣ ዋይ የሚለው ቁራ..."



የቁራ አባዜ ዘላለም "ዋይ! ዋይ!"
ዕንቁራሪቶች ግን አንዱ ካንዱ ላይ
"ዕልል! ዕልል!" ሲሉ፣ ተቃቅፈው ስናይ
ምስጢሩ ምንድነው፣ ይደንቅ የለም ወይ?



ዝናብ በዘነበ፣ ባካፋ ቁጥር
የመልካቸው ብዛት፣ ምድረ ጓጉንቸር
ከያለበት ወጥቶ ይላል ቱር! ቱር!
ወዳጁን ፍለጋ ለዘፈን፣ ለፍቅር...



በየኩሬውና በየወንዛ-ወንዙ
ሲበሉ፣ ሲባሉ፣ ሲዘዝልሉ፣ ሲያፌዙ፣
ሲዘፍኑ፣ ሲዳሩ፣ ዳንኪራን ሲያበዙ፣
ውሃው ደረቀና አለቁ፣ ጠነዙ...




ከዛፉ ላይ ወርዶ የተራበው ቁራ
እየተላቀሰ፣ ጮኾ እየተጣራ
ሬሳቸውን ሲለቅም፣ ዕንባውን ሲያጠራ
"ዋይ! እኔን" እያለ፣ ደግሞም እያቅራራ...

"ዋይ! ስል እኖራለሁ ያዘንኩኝ ይመስል
ትላልቁን ስመርጥ፣ ሳነሳና ስጥል
ላባ ተሸፋፍኖ ባይታይም ሆዴ
አረ እንዳልፈነዳ፣ ወይ ጉዴ! ወይ ጉዴ!"



"ላጭር ቀን ዘፍናችሁ እንዲህ ማለፋችሁ
ዋይ! ዕንቁራሪቶች ይህ ሆነ ትርፋችሁ!
የኔ አይሻልም ወይ፣ ረዥሮሙ ዘመኔ
ዋይ! ዋይ! ብልም እኮ ገና አለኹኝ እኔ"



"ተመስገን አምላኬ ላሳየኽኝ ታምር
ጓጉንቸሮች ጠግበው ሲዘፍኑብኝ ነበር
ዛሬ ግን አለቁ፣ እኔም በላኋቸው
አደራ ድገመኝ፣ ለከርሞም አምጣቸው..."



ጓጉንቸር ቢያበዙ ዕልልታና ዘፈን
ስልጣኔው አልፎ ሲደርቅ እንደ ጐመን
ዋይ! ብሎ እሚኖረው ሓበሻ ለአሁኑ
ቢደመር፣ ቢቆጠር፣ ረዥሮም ነው ዘመኑ...

ገ/ኢ. ጐርፉ።